***<u>የቴዎድሮስ ካሳሁን ጠበቃ አቶ ሚሊዮን አሰፋ እና የአዲስ ነገር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ መስፍን ነጋሽ ዛሬ በ 5፡10 ላይ ፍ/ቤት ቀረቡ፡፡</u>***

ዳኛ ልዑል ገ/ማያም በፍርድ ሂደት ያለ ጉዳይ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፣ ችሎቴን ደፍራችኋል ሲሉ ትላንት እደከሰሷቸው እና በፖሊስ ተይዘው እንዲቀርቡ ማዘዛቸው ይታወሳል፡፡

የዳኛው ትዕዛዝ ተፈጻሚ ሆኖ ትላንት ከሰዓት በኋላ በጋዜጣው ዋና አዘጋጅ በዳኛው ቢሮ ቀርቦ ስለዜናው ማብራሪያ የሠጠ ሲሆን የቴድሮስ ጠበቃ ደግሞ 11፡00 ሰዓት ላይ በፖሊስ ተይዘው አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ማረሚያ ቤት እንዲያድሩ እና ለዛሬው ችሎት እንዲቀርቡ ተደርገዋል፡፡

ዳኛው አቶ ልዑል ፤ በአቶ ሚሊዮን ላይ ፍ/ቤት የአቃቤ ሕግን ቦታ ተክቶ ማስረጃ ቆጥሮ አቅርቦብኛል፣ ለደንበኛዬ እንዳልከራከር አግዶኛል፣ በሚሉና በሌሎች ምክንያቶች እከሳለሁ ብለሀል፣ ከሆስፒታል የቀረበው የአስክሬን ምርመራ ማስረጃ የተሳሳተ ነው ብለሃል፣ የጋዜጣ አዘጋጁም በፍርድ ሂደት ላይ ያለውን ጉዳይ በሚመለከት አስተያየት መስጠት እንደማይቻል በማገናዘብ ዜናውን መዘገብ አልነበረበትም ሲሉ በሚያስችሉት 8ኛ ችሎት ላይ ክሳቸውን በንባብ አሰምተዋል፡፡ የተከሳሽ ጠበቆች አቶ ወንድአወቅ አየለ እና አቶ አበበ አሳመረ በበኩላቸው ደንበኛቸው አቶ ሚሊዮን አሰፋ ለጋዜጣው የሰጡት ቃል ሲጠቃለል በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ አቀርባለሁ፣ በዳኛው ላይ ቅሬታ ስላለኝ እከሳለሁ የሚል ነው፡፡ ይህም በሕገ መንግስቱም ሆነ በፍርድ ቤቱ አሰራር መብት ነው፡፡ የሰጡት አስተያየትም የመናገር ነጻነታቸውን በመጠቀም በመሆኑ ፍ/ቤቱ በነጻ እንዲያሰናብታቸው ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

እንደ ጠበቆቹ ገለጻ ይግባኝ ማቅረብ መብት ነው ፍ/ቤቱም ይህንን ይፈቅዳል እራሱም ጠይቁ ይላል፡፡ ዳኛው ላይ ቅሬታ ካለም የዳኞች ጉባኤ ባወጣው የዲሲፒሊን ደንብ መሰረት መክሰስ ይቻላል፡፡ የዲሲፒሊን ቅሬታ ማቅረብም

ችሎትን እንደመድፈር እንደማስፈራሪያ እና ዛቻ ሊታይ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ችሎት መድፈር የሚባለው በችሎት ውስጥ ያልተገባ ተግባር መፈጸም ከፍርድ ቤቱ ውጪ የፍርድ አመራሩን ለማወክ የሚያስችል፣ ምስክሮችን የሚነካ፣ ማስረጃ የሚሰውር ተግባር አልፈጸሙም ዛቻ እና ማስፈራሪያ የሚባለውም ዳኛውን አስባርራለሁ፣ አስቀጣዋለሁ በሚል የተገለጸ ቢሆን ዛቻ እና ማስፈራሪያ ሊባል ይችል ነበር፡፡ ችሎት መድፈር የሚባለው ሀረግን በሀገራችንም ሆነ በውጭ የታወቁ የሕግ ማህደራት የሚተረጉመው በጠባቡ ነው፡፡ ስለዚህ ደንበኛዬ ዳኛው ላይ አልዛተም አልስፈራራም ችሎትንም አልደፈረም፡፡ ይልቅስ መሰረታዊ የሆነ መብቱን ነው የተጠቀመው ሲሉ የአቶ ሚሊዮን ጠበቃ አቶ ወንድአወቅ አየለ ተከራክረዋል፡፡

አቶ ልዑል በበኩላቸው በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይ ላይ እንደልብ መናገር ይቻላል እያሉ ነው፡፡ ብይን በተሰጠበት ማስረጃን እየተቸህ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ የዐቃቤ ሕጉን ሥራ ተክቷል ብለህ ተናግረሀል ይህ አግባብ አይደለም ከአንድ ባለሙያ ጠበቃ የሚጠበቅ ነውን? ሲሉ ክሳቸውን አጠናክረዋል፡፡

የተከሣሹ ጠበቃ በበኩላቸው በማስረጃዎቹ ላይ ብይን ስለተሰጠ አስተያየት መስጠት ይቻላል ደንበኛዬ ፍ/ቤቱ የአቃቤ ሕጉን ስራ ሰርቷል ማለቱ ከአንድ ባለሙያ የማይጠበቅ እና በጊዜው ስሜታዊ ከመሆን የተሰጠ ነው፡፡ ነገር ግን ሆን ብሎ ደንበኛዬን ጎድቶብኛል አላለም ብለዋል፡፡ ተከሣሹ አቶ ሚሊዮን በበኩላቸው ያነሷቸው ነጥቦች የይግባኝ ምክንያቶቼ ናቸው ዳኛው ባላለቀ ጉዳይ ይግባኝ አይጠይቅም ደንበኛህን አታዘናጋ ቢሉም ውሳኔውን የሚሰጠው ይግባኝ ሰሚው ነው፡፡ ለዚህም በወንጀለኛ መቅጫ 141 ላይ የተሰጠኝ መብት በመሆኑ ይግባኙን አቀርባለሁ ብለዋል፡፡

የአዲስ ነገር ዋና አዘጋጅ አቶ መስፍን በበኩላቸው ዳኛው ትናንትና በዋስ እንደሚለቁኝ ቃል ገብተውልኝ ነበር፡፡ ስለዚህ የዋስትና መብቴን ጠብቁልኝ ሲሉ

ጥያቄ ቢያቀርብም ዳኛው አቶ ልዑል ጉዳዩን ለነገ ሐምሌ 30 ለጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በይደር ቀጥረውታል፡፡ ችሎትን መድፈር በሃገራችን ብቻ  የፍ/ቤት አሰራር መሰረት ከሦስት እስከ ስድስት ወር የሚሆን የእስር ቅጣት የሚያሰጥ ሲሆን ነገ የፍ/ቤቱ የሥራ ዘመን ማብቂያ መሆኑ ዳኛው የሚሰጡት ውሳኔ በጉጉት የሚጠበቅ እንዲሆን አድርጎታል፡፡